# የኢንዱስትሪ ዘርፍ የ2009 በጀት አመት

# የዘጠኝ ወር እቅድ አፈጻጸም፤

መጋቢት 2009 ዓ.ም

ባህርዳ

## መግቢያ፤

የኢንዱስትሪ ልማቱ ዕድገት እንደሃገር በተለይ ደግሞ እንደ ክልል በጅምር ላይ የሚገኝ ነው፡፡ የዘርፉን ልማት በማፋጠን የአገሪቱንና የክልሉን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ማኅሻ መርሆዎችን የተከተለ አገራዊና ክልላዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

በክልላችን ኢንዱስትሪላይዜሽንን ለማስፋፋት ከሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመነሳት የ2009 በጀት ዓመት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ለኢንዱስትሪ ልማት መሠረት የሆኑትን አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ለማድረግ ጥረቶች ተጀምረዋል፡፡ የኢንዱስትሪ አደረጃጀት ወደ ወረዳና ከተሞች እንዲወርድ በማድረግ የገጠር ኢንደስትሪያላይዜሽን ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት ተጀምሯል፡፡ ክላስተር ማእከላትን፣ ኢንዱስትሪ መንደሮችንና ኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማልማት ለኢንዱስትሪ ማስፋፋት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ያልተፈቱና መፈታት ያለባቸው ከአማካከት፣ ከግንዛቤ፣ ከክህሎት፣ ከአደረጃጀትና አሰራር እንዲሁም ከግብዓት አቅርቦት አኳያ በአመራሩ፣ በባለሙያወና በባለሃብቱ በኩል የሚስተዋሉ ችግሮች አሉ፡፡ ከዚህ አኳያ የ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የቀጣይ ትኩረት ጉዳዮች በሚከተለዉ መልኩ ቀርቧል፡፡

## ክፍል አንድ፤ የ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም እስከ አሁን ያለበት ደረጃ

ከበሮው የሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የተቀዳ የዘርፍ ዕቅድ በማዘድ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን እቅዱንም በየደረጃው ለሚገኙ አመራርና ባለሙያዎች፣ አጋር አካላት፣የልማት ድርጅቶችና

ብዙሃን ማሕበራት መድረክ ተዘጋጅቶ ወይይት በሚድረግ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ የተዘጋጀዉን ዕቅድና የተደረሰበትን መግባባት መሠረት ያደረገ የዕቅድ አፈጻጸም ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2.1.አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን አቅም ለማሻልበት የተከናወኑ ተግባራት

1. በበጀት ዓመቱ የ2469 የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ችግር ለማየት እቅድ ተይዞ በስምንት ወር ወስጥ የ601 አምራች ኢንዱስትሪዎች ያሉባቸዉን ችግሮች ተለይቷል፡፡ አፈጻጸሙ 24.3 ፐርሰንት ነው፡፡
   - ❖ በአግሮፐሮሰሲንግ፣ምግብና ፋርማሲቲካል ዘርፍ አነስተኛ 31፣መካከለኛ 95፣ከፍተኛ 21፤ በድምሩ 147፤
   - ❖ በጨ/ጨርቅና ቆዳ ዘርፍ አነስተኛ 89፣መካከለኛ 21፣ከፍተኛ 15፤በድምሩ 125፤
   - ❖ በብረታብረትና እንጨት ዘርፍ አነስተኛ 94፣መካከለኛ 212፣ከፍተኛ 23፤በድምሩ 329፤ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ችግር ተለይቷል፡፡
   - ✓ ይህ ከላይ የተገለጸው አፈጻጸም ከማስም በላይ ወስጣዊ ችግሮችን ማጥናት ላይ ያነጣጠረ መሆን ሲገባው አብዛኛው ተጠንቶ ተለዩ የተባሉት ችግሮች ውጫዊ ሆነው ተገኝተዋል፡፡
2. ችግራቸው የተለየላቸዉን ኢንዱስትሪዎች መቶ ፐርሰንት ለመፍታት እቅድ ተይዞ፡(147/601) 24.5 ፐርሰንት የሚሆኑ ኢንዱስትሪወች ብቻ የተወሰኑት ችግሮቻቸው ተፈትቶላቸዋል፡፡ የነዚህን የተፈቱ ችግሮችን ስናየው ወጣት አስመዝጋቢዎች ዋና ተዋናይ የዘርፉ ባለሙያወች ጥረት አናሳ እንደነበር ለማንዘብ ችለናል፤

   በዘርፍ ነጥለን ስናየው ደግሞ እንደሚከተለው ነው፡፡
   - ❖ በአግሮፐሮሰሲንግ ምግብና ፋርማሲቲካል ዘርፍ አነስተኛ 2፣መካከለኛ 40፣ከፍተኛ 7፤በድምሩ 49፤
   - ❖ በጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ዘርፍ አነስተኛ 1፣መካከለኛ 11፣ከፍተኛ 9፤በድምሩ 21
   - ❖ በብረታብረትና እንጨት ዘርፍ አነስተኛ 24፣ መካከለኛ 45፣ ከፍተኛ 17፣ በድምሩ 86 ኢንዱስትሪዎች ችግር ተፈትቷል፡፡
3. የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም በተመለከተ ወደ 76 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ
   - ❖ በአግሮፐሮሰሲንግ፣ምግብና ፋርማሲስቲካል 63.5 በመቶ(የ14 ኢንዱስትሪወች ብቻ)
   - ❖ ጨርቃጨርቅና ቆዳ 58.46 በመቶ(የ7 ኢንዱስትሪወች ብቻ)፣
   - ❖ ብረታብረተረና እንጨት 72 በመቶ ሲሆን፣
   - ❖ በአማካይ 64.65 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡
   - ✓ በዚህ ተግባር ዙሪያ ስራው በእምነት ተይዞ እየተተገበረ ነበር ማለት አይቻልም፡፡ ይህን ለማለት የደፈርነው ደግሞ የማምረት አቅም ምን ማለት እንደሆነ እንኳን ስናነሳ የዘርፉ

ሞያተኞች እኩል የሆነ እውቀትና ግንዛቤ አልነበረንም፡፡ አንዳንዶቹ አሁን ኢንዱስትሪው እያሚተ ያለው ሲካፈል ለሚሚረት ከቀደው ጋር እያወዳደሩ ሲሆን፣ሌሎች ደግሞ ኢንዱስትሪዉች ከዚህ ደርሰናል የሚሉትን ብቻ ይዘው ሪፖርት ይልካሉ፡፡

**4. የሥራ እድል ፈጠራን በተመለከተ፡**

በበጀት ዓመቱ በአነስተኛ እንዱስትሪዎች ለ4450 ዜጎች፣በመካከለኛና በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ለ12503 ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ በስምንት ወር ወስጥ ለ8300 ዜጎች የስራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን አፈጻጸማችን በዘርፍ ስናይ፡-

- በጨርቃጨርቅና ቆዳ ዘርፍ 556 በአነስተኛ፣ 345 በመካከለኛ፣ 941 በከፍተኛ፣ በድምሩ ለ1842 ዜጎች፣
- በአግሮፕሮሰሲንግ፣ምግብና ፋርማሲስቲካል ዘርፍ 345 በአነስተኛ፣1890 በመካከለኛ፣1289 በከፍተኛ፣በድምሩ ለ3524 ዜጎች፣
- በብረታብረትና እንጨት ዘርፍ 719 በአነስተኛ፣1470 በመካከለኛ፣745 በከፍተኛ፣በድምሩ ለ2934 ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

✓ በዚህ ተግባር ዙሪያ እኛ ሙተኞች የነበረን አስተዋጽኦ ምን ነበር ብለን ራሳችን ብንጠይቅ ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት ወጤት ስለሆነ ሚሉሱን በግልጽ እናገኘዋለን፡፡

5. ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋምና ማስፋፋት በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 491 አነስተኛ፣95 መካከለኛ፣13 ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ፡-

- ❖ በአግሮፕሮሰሲንግ፣ ምግብና ፋርማሲስቲካል መካከለኛ 84፣
- ❖ በጨርቃጨርቅና ቆዳ መካከለኛ 7 ከፍተኛ 3፣ በድምሩ 10፣
- ❖ በብረታብረትና እንጨት አነስተኛ 1፣ መካከለኛ 91፣ ከፍተኛ 13 በድምሩ 105፣
- ❖ በድምሩ አነስተኛ 1 መካከለኛ 182 ከፍተኛ 16 የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የኢንበስትመንት ፍቃድ አወጥተው ወደዘርፉ ተቀላቅለዋል፡፡

✓ ነገር ግን የኢንበስትመንት ፈቃድ ከአወጡ በኋላ የእኛ ክትትልና ድጋፍ በጉልህ ያሻቸዋል፡፡ በመሆኑም የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ምን ላይ እንደደረሰ በየዘርፉ ለይተን ድጋፍና ክትትል በሚድረግ እንቅፋቶችን ማየትና መፍታት ይኖርብናል፡፡

## 2.2. አነስተኛ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ከማጠናከር አንፃር የተከናወኑ ተግባራት

በበጀት ዓመቱ ለ71 አነስተኛ፣ለ17 መካከለኛና ለ7 ከፍተኛ በድምሩ ለ95 አምራች ኢንዱስትሪዎች የካይዘን ስርዓትን ለማስተግበር ታቅዶ

- ❖ በጨርቃጨርቅና ቆዳ ዘርፍ አነስተኛ 27 መካከለኛ 2 ከፍተኛ 2፣በድምሩ 31፤
- ❖ በአግሮፕሮሰሲንግና ምግብ ዘርፍ አነስተኛ 4፣መካከለኛ 6፣ከፍተኛ 3፣ በድምሩ 13፤

- ❖ በብረታብረትና እንጨት መካከለኛ 6 ከፍተኛ 4 በድምሩ 10 ኢንዱስትሪዎች በመተግበር ላይ ናቸው፡፡

ለአነስተኛ 19 ለመካከለኛ 12 በድምሩ 31 ኢንዱስትሪዎች አዋጭ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በምግብና አግሮ ፕሮሰሲንግ የ19 ኢንዱስትሪዎች ፍላጎት ተለይቷል፡፡

ኢንዱስትሪዎችን ከማሽልጠን አኳያ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ ለ315 አነስተኛ፣ለ130 መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የቴክኒክና ኢንተርፕነርሽፕ ስልጠና እንዲያገኙ ታቅዶ በብረታብረትና እንጨት አነስተኛ 100፣ መካከለኛ 14፣ በአግሮፕሮሰሲንግና ምግብ 34 ኢንዱስትሪዎች የኢንተርፕነርሽፕ ስልጠና ፍላጎት ተለይቷል፡፡

- ✓ የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ማለት አራቱን የድጋፍ ማዕቀፎች ስራ የያዘ መሆኑ ቢታወቅም ገና ቆርጠን ያልገባንበት ስራ መሆኑ ለማንም ግልጽ ጉዳይ ነው፡፡ ምንም እንኳን ይህን ስራ የሚሰለጥልንን ዩኒቨርሲቲዎችንና ቴ/ሙ/ኮሌጆችን የትስስር ስራ በማስራትና የጋራ እቅድ በማቀድ ጀምር ስራዎች ቢኖሩም ወደ ተግባር ያለደረሰ ስራ ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡

## 2.3 ሊዝ ፋይናንስና ፕሮጀክት ፋይናንስን በተመለከተ

በበጀት ዓመቱ ለ438 አነስተኛ እና ለ100 መካከለኛ በድምሩ ለ538 አምራች ኢንዱስተሪዎች የማሽን ሊዝ ከራይ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታቅዶ፡

- ❖ በብ/ብረትና እንጨት አነስተኛ 18 መካከለኛ 140፣ድምር 158
- ❖ በጨርቃጨርቅና ቆዳ አነስተኛ 47፣ መካከለኛ 7፣ከፍተኛ 7፣ በድምሩ 61
- ❖ በአግሮፕሮሰሲንግና ምግብ ዘርፍ መካከለኛ 108
- ❖ በድምሩ አነስተኛ 31 መካከለኛ 257 ኢንዱስሪዎች ፍላጎት ተለይቷል፡፡

**ከዚሁ ወስጥ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንዱስትሪዎች**

- ➢ በብረታብረት አነስተኛ 13 መካከለኛ 17፣በድምሩ 30፣ከዚህ ወስጥ 19 ከዋልያ የካፒታል እቃዎች ተጠቃሚ ሲሆኑ በካፒታል ደረጃ ሲሰላ 8,412,673 ብር ነው፡፡ 11 ኢንዱስትሪወች ደግሞ በልማት ባንክ ተጠቃሚ ሲሆኑ በካፒታል ደረጃ ሲሰላ 41,430,000 ብር ነው፡፡
- ➢ በጨርቃጨርቅና ቆዳ አነስተኛ 25፣ መካከለኛ 4፣ ከፍተኛ 2 በድምሩ 31 ሲሆኑ፣ከዚህ ወስጥ 24 ኢንዱስትሪዎች በዋልያ የካፒታል እቃወች ተጠቃሚ ሲሆኑ በካፒታል ደረጃ ሲሰላ 1,941,104.55 ብር ነው፡፡ 7 ኢንዱስትሪወች ደግሞ በልማት ባንክ ተጠቃሚ ሲሆኑ በካፒታል ደረጃ ሲሰላ 93,425,498 ብር ነው፡፡

- በአግሮ ፕሮሰሲንግና ምግብ አነስተኛ 8፣ መካከለኛ 4 በድምሩ 12 ኢንዱስትሪዎች ተጠቃሚ ሲሆኑ፣ከዚህ ወስጥ 8 ኢንዱስትሪዎች በዋልያ የካፒታል እቃወች ተጠቃሚ ሲሆኑ በካፒታል ደረጃ ሲሰላ 549,530.00 ብር ነው፡፡ 4 ኢንዱስትሪወች ደግሞ በልማት ባንክ ተጠቃሚ ሲሆኑ በካፒታል ደረጃ ሲሰላ 27,103,826 ብር ነው፡፡
- በጠቅላላ 426 ኢንዱስትሪዎች የማሽን ሊዝ ከራይና የፕሮጀክት ፋይናንስ ጥያቄ ካቀረቡት መካከል 73ቱ ተጠቃሚ ሲሆኑ፣ከተጠቃሚት ወስጥ 51ዱ በዋልያ የካፒታል እቃወች ፋይናንስ አክሲወን ማህበር የተጠቀሙ ሲሆን፣በካፒታል ሲተመን 10,903,307.6 ብር ነው፡፡ በልማት ባንክ ደግሞ 22ቱ ኢንዱስትሪወች ተጠቃሚ ሲሆኑ፣የማሽኖችና የፕሮጀክቶች ዋጋም 161,959,324 ብር ይሆናል፡፡

## 3. የተለያዩ ባለሃብቶችን ግንዛቤ የመፍጠር ስራን በተመለከተ

- በክልላችን ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት በመጀመሪ ደረጃ ሃብት ያላቸወን የህብረተሰብ ክፍሎች በማለየት በበጀት አመቱ 7500 ለሚሆኑ ባለሃብቶች ግንዛቤ ለመፍጠር እቅድ ተይዞ እስካሁን ባለው ለ4347 ባለሃብቶች ግንዛቤ ለመፍጠር ተችሏል፡፡

- ለ601 ሞዴል አርሶ አደሮች፣
- ለ1195 በጥ/አነስተኛ ለተሰማሩና ለተሸጋገሩ፣
- ለ2264 በንግድና አገልግሎት ዘርፍ ለተሰማሩት፣
- ለ215 ኮንትራክተሮች፣
- ለ72 ከክልል ውጭ ላሉ ባለሃብቶች
- በድምሩ ለ4347 ባለሃብቶች ግንዛቤ ተፍጥሯል፡፡

- ግንዛቤው ያመጣውን ለወጥ በምናይበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሱት ስራዎች ሁሉ ለምሳሌ ለ426 ባለሃብቶች የሊዝ ፋይናንስ ፍላጎት እንዲያሳድሩና 73ቱ ወደ ተጠቃሚነት እንዲሸጋገሩ፣እንዲሁም 199 የሚሆኑ ባለሃብቶች ወደ ዘርፉ እንዲቀላቀሉና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማውጣት እንዲችሉ አድርጓል፡፡ በተለይም በዚህ እንቅስቃሴ በጥሩ ሁኔታ የሚለጹ ዞኖች ሰሜን ጎንደር፣ጎንደር ከተማ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደሴ የተሻሉ ናቸው፡፡

## 4. የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ያለበት ሁኔታ

በበጀት ዓመቱ ቅድመ ግንባታ ላይ የሚገኙትን 622 ፕሮጀክቶችን ወደ ግንባታ ለማስገባት ታቅዶ በእንጨትና ብረታብረት ኢንዱስትሪ 100፣ በጨርቃ ጨቅና የቆዳ ኢንዱስትሪዎች 19፣ በአግሮፕሮሰሲንግ

ኢንዱስትሪ 82 በድምሩ 201 የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን በስምንት ወር ወስጥ ወደ ግንባታ ማስገባት ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ ወደ ግንባታ የገቡትን 241 የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ ወደ ማምረት እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ በ8 ወሩ ወስጥ ወደ ማምረት የገቡ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች በእንጨትና ብረታብረት ኢንዱስትሪ 27፣ በጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ኢንዱስተሪ 4፣ በአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ 19 በድምሩ 48 የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ወደ ማምረት ደረጃ ማሸጋገር ተችሏል፡፡

እነዚህን ሁለት ተግባራት ለማስፈጸም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ያሉ ሞያተኞች ዘንድ የተግባር የባለቤትነት ጥያቄወች በስፋት እየተነሱ ተግባራትን የማፈፋት ዝንባሌ የታየበት ነበር ብሎ መወሰድ ይቻላል፡፡

በማሆኑም በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን እየደገፉ ወደ ማምረት ስራ እንዲገቡ በማድረግ ረገድ በየደረጃው ያለ አመራር የሚሰጠው ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ሆኖ ፈቃድ አወጥተው ወደ ግንባታ ለመግባት በዝግጅት ላይ ያሉ፤ ወደ ግንባታ የገቡ እና ግንባታ አጠናቀው በማስረተ ልማት ችግር ወደ ማምረት ስራ ያልገቡ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ክትትል እያደረጉ የሚላቸውን በማሟላት ወደ ማምረት ስራ እንዲሸጋገሩ በማድረግ ረገድ እየተገማመ ያልተሟ ተግባር በማሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በማሆን ወደ ስራ መግባት ይጠይቃል፡፡

## 5. የማምረቻና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች የወጪ ምርትን በአይነትና የወጪ ምንዛሬ ገቢን ከማሳደግ አኳያ

በበጀት ዓመቱ የወጪ ምርትን በአይነት ከ16 ወደ 28 በማሳደግ አምራች ኢንዱስትሪዎች አሁን ለውጭ ምንዛሬ ገቢ እያበረከቱ ካሉት 16.4 ሚሊዮን ዶላር ወደ 20.5 ሚሊዮን ዶላር ለማሳደግ ታቅዶ፡-

- ❖ በጨርቃጨርቅና ቆዳ ዘርፍ የወጪ ምርትን በአይነት ወደ 12 ማሳደግ የተቻለ ሲሆን የተገኘ ገቢ 7 ሚሊዮን ዶላር ነው፡፡
- ❖ በአግሮፕሮሰሲንግ፣ምግብና ፋርማሲቲካል ዘርፍ በአይነት የተቀማጠውን ግብ ማሳደግ አልተቻለም በዚህም ማስረት የተገኘ ገቢ 3.873086 ሚሊዮን ዶላር ብቻ ነው፡፡ በድምሩ ሲታይ በአይነት ከነበረው 16 የምርት ዓይነት 10.873086 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡
- ❖ በዚህ ተግባር አፈጻጸም ላይ የእኛ ሞያተኖች ለኢንዱስትሪወች ያደረጉት ድጋፍና ክትትል በጉልህ የሚታይ አይደለም፡ ይልቁንም የኤክስፖርት ሽያጩ ከገቢወችና ጉሙሩክ ቅርንጫፎች ሚጃ በመቀበል ሪፖርት ሰርቶ የመላክ ተግባር ላይ ማዙኮር ይበዛል፡፡

### 5.1. ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶችን በማሟላት የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ፤

በክልላችን ኢንዱስተሪላይዜሽንን ለማስፋፋት ከመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ጀምሮ የኢንዱስትሪወን ዘርፍ በአዲስ በሚደራጀት ወደ ስራ ለማስባት ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ከክልል እስከ ክላስተር ሜከላት ለኢንዱስተሪያሊስቶቹ የኢንዱስትሪ አክስቴንሽን ድጋፍ ሊሰጥ የሚችለል ተቋም እና ሞተኛ በሚደራጀት እንዲሁም ባለሀብቶቹ እንደ ካፒታል፣ እወቀትና አቅማቸው ሊያለሙ የሚችሉበት የኢንዱስተሪ ፓርክ እና የኢንዱስተሪ ክላስተር ሜከላት ሊሆን የሚችል ሜሬት በማዘጋጀትና ማሰረተ ልማት በማሟላት በመንግስት በኩል ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተከናወነዋል እየተከናወኑም ይገኛሉ፡፡

በዚህም ማሰረት በክልሉ በ20 ከተሞች በፌደራል መንግስት የሚለሙ አምስት የአግር ፕሮሰሲንግና ሁለገብ ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ በክልሉ መንግስት የሚለሙ 28 ሁለገብ የኢንዱስተሪ ፓርኮች/መንደሮች/ እና አንድ የአግሮ ፕሮሰሲንግ የኢንዱስትሪ ልማት ፓርክ፣ 21 የክላስተር ሜከላት በመንግሰት በጀት ድጋፍ ማሰረት ልማት የተሟላላቸው መሆኑንና እየተሟላላቸዉም እንደሆነ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

በሌላ በኩል በክልሉ በሚገኙ በሁሉም ከተማ አስተዳደርና ወረዳ ሜከላት ለኢንዱስተሪ ክላስተር ሜከላት ለትላልቅ ከተሞች 250ሄ/ር፣ ለአነስተኛ ከተሞች100ሄ/ር፣ እንዲሁም ለወረዳ ሜከላት 50ሄ/ር ሜሬት ማዘጋጀት እንዳለበት ለዞን፣ከተማ አስተዳደርና ወረዳ አመራር ጋር በመግባባት ተግባሩ ወደ ዞን፣ከተማ አስተዳደር/ወረዳ/ እንዲወረድ ተደረጎ በሂደት ላይ ይገኛል የእያንዳንዱን ተግባር አፈጻጸምም በሪፖረት ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

ይሁን እንጅ በመንግስት በኩልም ሆነ በግሉ ዘርፍ ያልተፈቱና ሚፈታት ያለባቸው ችግሮች ያሉ መሆኑን ከዞኖች እና ከተማ አስተዳደርች አፈጻጸም ሚረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከአመላካከት፣ አሰራርና አደረጃጀት፣ እወቀትና ክህሎት እንዲሁም ከግብዓት አቅርቦት አኳያ በአመራሩ፣ በሞተኛወና በራሱ በግል ባለሀብቱ ማሰረታዊ የሆኑ ችግሮች መኖራቸዉን በክልሉ በሚገኙ ዞንችና ከተማ አስተዳደሮች በተላከው ሳምንታዊና ወርሃዊ ሪፖርት ሚረጋገጥ ችለናል ፡፡

## 2. በፌደራልና በክልሉ መንግስት የሚለሙ ትልልቅ ሁለገብና የአግሮ ፕሮሰሲንግ የኢንዱስተሪ ፓርኮች አፈጻጸምን በተመለከተ

በክልላችን 5 የኢንዱስተሪ ፓርኮች በደበር ብርሃን፣መንጃር አረረቲ፣ኮምጥልቻ፣ቡሬና በህርዳር የተከለሉ ሲሆን ምንጃር አረርቲ፣ኮምጥልቻና ባህርዳር በፌድራል መንግስት የሚለሙ በበመሆናቸው የከሞጥልቻ በግንባታ ሂደት ሚገኝ ሲሆን ምንጃር አረርቲ ቦታወን በሚጽዳት ሂደት ላይ ይገኛል በህርዳ ቦታ የመካለል ስራ ብቻ ተከናዉኗል በሌላ በኩል በክልሉ የሚለማው የቡሬ የተቀናጀ አግር ኢንዱስትሪ ፓርክ 250ሄ/ር ሜሬት ከሶስተና ወገን ነፃለሚድርግ የካሳ ስሌት ተሰርቶ የተጠናቀቀና በጀቱ ወደ ታች ወረዶ ለባለይዞታዎቹ ካሳ በመክፈል ላይ ሲሆን የማሰረተ ልምት ግንባታ ስራም ተጀምሯል፡፡

## 3. ነባር ሁለገብ የኢንዱስትሪ ፓርክ/ማንደር/ አፈጻጸም

በ20 ከተሞች ወስጥ 28 ሁለገብ ኢንዱስተሪ ፓርኮች /ማንደሮች በነባር1921.884 ሄ/ር በአዲስ 213ሄ/ር በድምሩ 2134.884 ሄ/ር ሜሬት የተከለለ ሲሆን ከዚህ ወስጥ በሁሉም ከተሞች ከሶስተኛ ወገን የጸዳ 1676.194 ሄ/ር ሜሬት ይገኛል ከሦስተኛ ወገን ከፀዳው ሜሬት ወስጥም ለ857 ፕረጀክቶች 808.177 ሄ/ር በ14 ከተሞች ለባለሀብት ተላልፏል ቀሪዎቹ 6 ከተሞች ሰሜን ጎንደር ደባርቅ ከተማ አስተዳደር፣ ሰሜን ወሎ ቆቦ ከተማ አስተዳደር፣ ሰሜን ሸዋ ሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር፣ ደቡብ ጎንደር ወረታና ነፋስ መውጫ ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ደሴ ከተማ አስተዳደር ሁለገብ የኢንዱስትሪ ፓረርኩን/ማንደሩን ከመከለል ባለፈ ቦታዉን ከሶስተኛ ወገን አጽድቶ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኩ/ማንደሩ ፕሮጀክት ሜልምሎ ማስገባት በኩል ችግር ያለባቸው በመሆኑ እከአሁን ለሜልማት የገባ ፕሮጀክት የለም፡፡

በሌላ በኩል ወደ ሁለገብ ኢንዱስትሪ ፓርኩ ከገቡት 857 ፕሮጀክቶች ወስጥ 293 ፕሮጀክቶች በወላቸው ማሰረት ወደ ግንባታ ያልገቡ ሲሆን ከነዚህም ወስጥ 101 ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ባለምግባታቸው 80.382 ሄ/ር ሜሬት እንዲነጠቁና ሜሬቱ ወደ ሜሬት ባንክ እንዲመለስ ተደርጓል ከዚሁ ጋር በተያያዘ ግንባታ ካጠናቀቁትና ከተለዩት 271 ፕሮጀክቶች ወስጥ 61 ፕሮጀካቶች ወደ ማምረት የተሸጋገሩ ሲሆን ቀሪዎች 114 ፕሮጀክቶች በተለያየ ምክንያት ወደ ምርት ማምረት ያልገቡ ወይም ጀምረው ያቋረጡ በመሆናቸው በሚቀጥለው ዘርፉን በሚመራው ተቋም ጠንካራ የኢንዱስትሪ አክስቴንሽን ድጋፍና ክትትል ያስፈልጋቸዋል፡፡

## 4.በአራቱ ትልልቅ ከተሞች በነባር ሁለገብ ኢንዱስተሪ ፓርክ ለኢንቨስትመንት ሜሬት የወሰዱ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የጥናት ምልከታ/ ባ/ዳር፣ጎንደር፣ኮምቦልቻና ደ/ብርሃን/

የክልሉ ንግድ ኢንዱስተሪ ገበያ ልማት ቢሮ በክልሉ የሚገኙ በርካታ ፕሮጀክቶች የሚገኙባቸዉን ሁለገብ የኢንዱስተሪ ፓርኮች ከተለያዩ ቢሮና ከራሳቸው ከተማ አስተዳደሮቹ በተወጣጡ ኮሚቴዎች ባ/ዳር፣ ደብረ ብርሃን፣ ኮምቦልቻና ጎንደር እንዲጣና በሚድረግ የአራቱንም ከተማ አሰተዳደሮች የኢንቨስትመንት ሜሬት አፈጻጸም ስንመለከት ወደ ሁለገብ ኢንዱሰሪ ፓርኩ /ማንደሩ የገቡ ፕሮጀክቶች 504 ሲሆኑ ከዚህ ወስጥ ባዶ ቦታ ይዘው የተቀመጡ 233(46.2%)፣ በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ 96(19%)፣ ግንባታ ያጠናቀቁ

175(34.72%) ፕሮጀክቶች ሲሆኑ ከነዚህም ወስጥ 61(12.1%) ፕሮጀክቶች ሙሉ አቅማቸው ባይሆንም እንኳ ማምረት ላይ ያሉ ናቸው ቀሪዎቹ 114(22.6%) ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በተላያየ ምክንያት ወደ ማምረት ያልገቡ /ጀምረው ያቋረጡ በመሆናቸው ዘርፉን የሚመራው ተቋም ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በማዘርጋት ወደ ምርት ለመግባት የሚያስችሉ ትግዳሮቶችን በማለየት የኢንዱስትሪ ኤክስንቴሽን አገልግሎት በማስጠት ወደ ምርት ማስገባት ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡

ይሁን እንጅ በተለያየ የማስረተ ልማት አለመሟላትና በሌላም ድጋፍ ችግር ወደ ግንባታ ያለገቡና ግንባታ አጠናቀው ምርት ማምረት ያልጀመሩ ፕሮጀክቶች ተለይተው ለሚመለከተው እንዲደረስ የተደረገ ሲሆን ከዛ ውጭ በሆነ በራሳቸው ምክንያት በገቡት ወል ማስረትወደ ግንባታ ያልገቡ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የየከተማ አስተዳደሩ አመራር አሰራሩን ተከትሎ መሬቱን ወደ መሬት ባንክ እንዲያስመልስና ወደ ልማት እንዲገባ ስምምነት ላይ ተደረሰ ሲሆን በከፍተኛ አመራሩ ተገምግሞ አቅጣጫ ሲሰጥበት ወደ ተግባር እንደሚገበ ታሳቢ ተደረጎ ወደፊትም ክትትል የሚጠይቅ እንደሆነ በተቀመጠው አቅጣጫ ማስረት ወደ ግንባታ ባልገቡ ፕሮጀክቶች ላይ ከተማ አስተዳደሮቹ ከማስጠንቀቂያ ጀምሮ ወደ መሬት ባንክ እስከ ማስመለስ እርምጃ የጀመሩ መሆናቸውን በሪፖርት የተገለጸ በመሆኑ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እና ወደ ምርት ማምረት ባልገቡ ፕሮጀክቶች ላይም ችግራቸውን ለይቶ የመፍትሄ አካል ሊሆን የሚችል የክትትልና ድጋፍ ስርአትና የኢንዱስትሪ ኤክስንቴሽን ማዘርጋት ተገቢ ይሆናል፡፡

## 5. በአዲስ ለኢንዱስትሪ ክላስተር የሚዘጋጅ መሬትን በተመለከተባለ

### ሀ. ለዞንና ሌሎች 250 ሄ/ር መሬት የሚያዘጋጁ ከተሞችን በተመለከተ

በክልል በሁሉም አካባቢ ያሉ የዞንና ተመሳሳይ መካከለኛ ከተሞች ለኢንዱስትሪ ክላስተር ሚከላት 250 ሄ/ር መሬት እንዲያዘጋጁ ከወረዳ ዞንና ከተማ አስተዳደር አመራሮች ጋር መግባባት ተደርሶ ወደ ታች የወረደ ሲሆን እስከዚህ ሳምንት ማጠናቀቂያ ወደ ተግባር የገቡ ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ጎንደር ከተማ አስተዳደር፣ ምስራቅ ጎጃም ደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር፣ ሰሜን ሸዋ ዞን ደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር፣ ደቡብ ጎንደር ደብረታቦር ከተማ አስተዳደር፣ ባህረዳ ከተማ አስተዳደር፣ አዊ ዞን እንጅባራ ከተማ አስተዳደር እያንዳንዳቸው 250 ሄ/ር መሬት ሲከልሉ ቀሪዎቹ ማለትም ምእራብ ጎጃም ዞን ፍኖተሳለምና ቡሬ ከተማ አስተዳደር፣ ደቡብ ወሎ ዞን ከንቦልቻ ከተማ አስተዳደር፣ ሰሜን ወለዞን ወልደያ ከተማ አስተዳደር፣ ወግ ኽምራ ሰቆጣ ከተማ አስተዳደርና ኦሮሞ ብሐየረሰብ ዞን ከሚሴ ከተማ አስተዳደር፣ እንዲሁም ደሴ ከተማ አስተዳደር አንዳንዶቹ ገና በእንቅስቃሴ ላይ ሲሆኑ ደሴ ከተማ አስተዳደር፣ ኦሮሞና ዋግ ኽምራ ዞንወደ ጭራሽ ወደ ተግባሩ አልገቡም፡

### ለ. በከተማ አስተዳደር ደረጃ 100ሄ/ር ሜት ለኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከላት የሚዘጋጅ ሜትን በተመለከተ

በክልሉ በከተማ አስተዳደር ደረጃ ለኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከላት እያንዳንዱ ከተማ አስተዳደር 100ሄ/ር ሜት እንዲያዘጋጅ ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን እስከዚህ ሳምንት ወደ ተግባር ገብተው ያጠናቀቁ 3 ዞኖችና 4 ከተማ አስተዳደሮች ማለትም ሰሜን ሸዋ ዞን ዓለም ከተማ ከተማ አስተዳደር፣ ደቡብ ጎንደር ዞን ወረታ ከተማ አስተዳደር፣ አዊ ዞን ዳንግላና ጃዊ ከተማ አስተዳደሮች ወደ ትግባሩ ገብተው የሜት ዝግጅቱን ያጠናቀቁ ሲሆኑ ቀሪዎቹም በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ ከነዚህ ውጭ ያሉ 7 ዞኖችና በዞኖቹ የሚገኙ ከተማ አስተዳደሮች ማለትም ሰሜን ጎንደር፣ ምስራቅ ጎጃም፣ ምዕራብ ጎጃም ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ አሮሞ ብሄረሰብ ዞንና ዋግ የሚገኙ ከተማ አስተዳደሮች አንዳንዶቹ ገና በእንቅስቃሴ ላይ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ዋግ ኽምራ፣አሮሞ ብሄረሰብ ዞን ወደ ተግባሩም ሊገቡ አልቻሉም በመሆኑም ተግባሩን ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ትኩረት ሰጥተው ሊከታተሉት ሜቱን ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡

### ሐ. በወረዳ ማዕከል ደረጃ 50ሄ/ር ሜት ለኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከላት የሚዘጋጅ ሜትን በተመለከተ

በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ወረዳ ማዕከላት ለኢንዱስትሪ ክላስተር እያንዳንዱ ወረዳ 50ሄ/ር ሜት እንዲያዘጋጅ ስምምነት ላይ ተደርሶ ተግባሩ በእቅድ ተይዞ ወደ ታች ወርዷል በእቅዳቸውም መሰረት ወደ ስራ የገቡ በሁለት ዞኖች የሚገኙ 4 ወረዳዎች ሲሆኑ እነርሱም ሰሜን ሸዋ ዞን ሞረትናጁሩ፣ መንዝጌራ፣ መንዝቀያና ምንጃር ሸንኮራ፤ ሰሜን ጎንደር ዞን ደንቢያ ወረዳ እንዳንዳቸው 50 ሄ/ር ሜት አዘጋጅተው አጠናቀዋል በእነዚህ ዞኖች የሚገኙ ሌሎች ወረዳዎችና በተጨማሪ ሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም ዞኖች እንዲሁም ደቡብ ጎንደርና አዊ ዞኖች በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኙ ቢሆንም ያለቀለት ሜት ማዘጋጀት አልቻሉም፡ ቀሪዎቹ ኦሮሚያ እና ዋግ ኽምራ ተግባር አልገቡም በአጠቃላይ አብዛኛዎቹ ዞኖችና ወረዳዎች ከእንቅስቃሴ ያለፈ ወደ ተግባር ገብተው ወጤት ማምጣት ባለመቻላቸው ለተግባሩ ትኩረት በመስጥት ከአጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር መድረክ ፈጥሮ በመነጋገር በአጭር ጊዜ ሜቱን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

### 6. በዚህ ዓመት ከሶስተኛ ወገን የሚፀዳ ሜትን በተመለከተ

### ሀ.የተቀናጀ የአግሮ ፕሮሰሲንግና ሁለገብ የኢንዱስተሪ ፓርክ፤

በዚህ በጀት ዓመት ማስፋፊያ የሚያስፈልጋቸውና ከሶስተኛ ወገን የሚጸዱ የአግሮ ኢንዱስትሪና ሁለገብ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በተመለከተ ሰሜን ሸዋ ደብረብርሃን ከተማ 100ሄ/ር፣ ምስራቅ ጎጃም ደጀን ከተማ 2ሄ/ር፣ ምእራብ ጎጃም ለቡሬ የተቀናጀ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ 74ሄ/ር ሰሜን ጎንደር ለገንዳ ወሃ

ከተማ 50ሄ/ር፣ለጎንደር ከተማ አስተዳደር20ሄ/ር፣ደቡብጎንደር ለደብረታቦር ከተማ አስተዳደር 20ሄ/ር፣ሰሜን ወሎ ለቆቦ ከተማ አስተዳደር1ሄ/ር እና ወልደያ ከተማ አስተዳደር 20ሄ/ር ደቡብ ወሎ ለከምባልቻ ከተማ አስተዳደር 50ሄ/ር በድምሩ 337 ሄ/ር ሜሬት ለሀለገብ የኢንዱስትሪ ፓርክ ለተቀናጀ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሜሬት ተከልሎ የካሳ ስሌት ተሰርቶ ከሶስተኛ ወገን እንዲጸዳና ለፕሮጀክቶች እንዲተላለፍ የተወሰነ ሲሆን ከኮምባላቻ ከተማ ውጭ ሁሉም ከተማ አስተዳደሮች በጠቅላላ በክልሉ 267ሄ/ር ሜሬት ሜሬቱን ለይተው ወደ ካሳ ስሌት/ግምት ስራ የገቡ ቢሆንም የካሳ ስሌቱን አጠናቆ በጀት የተለቀቀለት የቡሬ የተቀናጀ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ፓርክ 74 ሄ/ር ሜሬት ብቻ ሲሆን የደብረታቦር ከተማ አስተዳደርም 20 ሄ/ር ሜሬት የካሳ ስሌቱን አጠናቆ በቅርብ ቀን ለቢሮው ልኳል፡፡

**ለ. ኢንዱስተሪ ክላስተና ለገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት የተዘጋጅ ሜሬትን የካሳ ስሌት በተመለከተ**

በዚህ በጀት ዓመት ለኢንዱስተሪ ክላስተርና ለገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት በአዲስ/ ማስፋፊያ ከተከለሉት ሜሬት ወስጥ ከሶስተኛ ወገን የሚጸዱ የኢንዱስትሪ ክለስተር ማዕካላትና የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕካላት ሜሬትን በተመለከተ ሰሜን ሸዋ ዞን ደብረብርሃን ከተማ 20ሄ/ር፣ ሰሜን ወሎ ዞን ቆቦ ከተማ አስተዳደር 10ሄ/ር፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን ደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር 20ሄ/ር፣ ጎንደር ከተማ አስተዳደር 30ሄ/ር፣ ደቡብጎንደር ወረታ ከተማ አስተዳደር 20ሄ/ር፣ ባህርዳር ከተማ አሰተዳደር 100 ሄ/ር እንዲሁም ለሞጣ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት 9ሄ/ር በድምሩ 219ሄ/ር ሜሬት ለኢንዱስትሪ ክላስተርና ለገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት ተከልሎ የካሳ ስሌት ተሰርቶ ከሶስተኛ ወገን እንዲጸዳና ወደ ልማት እንዲገባ የተወሰነ ሲሆን ሁሉም ከተማ አስተዳደሮች ሜሬቱን ለይተው ወደ ካሳ ስሌት/ግምት ስራ የገቡ ቢሆንም የካሳ ስሌቱን አጠናቆ ወደ ክልል የላከ ከተማ ባለመኖሩ ስራው እንዲጓተት አድርጎታል በመሆኑም በመስክ በተግባባነው መሰረት እሰከ መጋቢት 20/2009 እንዲጠናቀቅ ጠንካራ ክትትል ያስፈልገዋል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ሪፖርት አስከተጠናከረበት እሰከ መጋቢት 15/2009 በጀት ዓመት ለቢሮው የደረሰን ሚረጃ የሚያመላክት ቢሆንም ሪፖርቱ በሁሉም ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች በማጠናከር በኩል ወስንነት ያለበት መሆኑ ተወስዶ በሪፖርት ታማኝነት በኩል የሚያጠራጥር ነገር ባይኖርም እንኳ የሁሉም ኢንዱስትሪ ፓረኮች ሪፖርት ሲጠናከር ሪፖረቱ ሊጨምር እንደሚችል ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡ በሌላ ሚሉኩ የባሕርዳር ከተማ አስተዳደር ለኢንዱስትሪ መንደር የታያዘ 100ሄ/ር ሜሬት ያለበት ደረጃና ከ የ2007 ከዚያ ወዲህ ያሉ የፕሮጅዮችን አፈጻጸም በሚረጃ እጥረት ምክንያት የሚያካትት መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡

## ክፍል ሁለት፡ ያጋጠሙ ችግሮች፤

ከክልል እስከ ዞንና ወረዳ ባለው መዋቅር የኢንዱስትሪ ዘርፍ አመታዊ እቅድ፣ የ2009 የቢ.ኤስ.ሲ ዕቅድ፣ የ1ለ5 እና ልማት ቡድን ዕቅዶች ተዘጋጅተው በየደረጃው ላለ አመራርና ሙያተኛ ግልጽነትና ተነሳሽነት በመፍጠር የኢንዱስትሪ ዘርፉን ለመደገፍ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተግባር ምእራፍ ለሙያተኛውና ለአመራሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በመፍጠር በአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያግዝ ተነሳሽነት ለመፍጠር ተሞክሯል፡፡

ይሁን እንጅ በበጀት ዓመቱ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች የአመለካከት፣ የክህሎት፣ የአደረጃጀት፣ አሰራር እና የግብአት አቅርቦት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### 3.1.1. ከአመለካከት አኳያ

- የኢንደስትሪ ዘርፉን ተግባር በትኩረት ይዞ አለመፈጸምና አመራሩንና ባለሙያ የኢንዱስትሪ ልማቱን ማጠንና በየደረጃው የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የእኔ ሜና የጎላ ነው ብሎ በእምነት አለመያዝ፣
- የሌሎችን አጋር አካላት አቅም አድርጎ ያለመጠቀም እንዲሁም የአመራሩን የሙያተኛውንና ወደ ዘርፉ የሚገባውን ባለሀብት አቅም የሚያሳድግ ግንዛቤ መፍጠር የአመራር ስራ አድርጎ አለመዉሰድ፣
- በዘርፉ የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር እና የኪራይ ሰብሳቢነት መንስኤና ምልክቶችን ለይቶ በዝርዝር ማስረጃ አስገድፎ ከመታገልና ከማረም ይልቅ ጉዳዮችን በቸልተኝነት የማለፍና ለኢንቨስትመንት መሬት ወስደው አጥረው የተቀመጡ ባለሀብቶችን ተቀራርጦ መሬቱን ለማስመለስ ጥረት ያለማድረግ
- በዕቅድ ላይ የተመሠረተ አፈጻጸምና ግምገማ እያካሄዱ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች የአፈታት ስልት እያስቀመጡ ያለመሄድና የተነሳሽነት መንፈስ አለመዳበር፣
- በጥቅም ማስደድ አባዜ እና በኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ድርጊት ራስን ነጻ አድርጎ ያለመንቀሳቀስና በትግሉ ላይም ያለመሳተፍ፣
- በአጠቃላይ በአሁኑ ሰዓት አመራሩም ሆነ ሙያተኛው ኢንዱስትሪን ለመምራት የሚያስችል ቁመና ላይ አይደለም፡፡ ይልቁንም የንግድ ዘርፍ ስራወች ላይ ብቻ መጠመድና የኢንዱስትሪውን ስራ ገሸሽ የማድረግ ዝንባሌ ይታያል፡፡

### 3.1.2. ከክህሎት–አኳያ

- ❖ የየአካባቢውን የመልማት አቅም ግምት ውስጥ ያስገባና አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን የሚያጠናክር እቅድ የማዘጋጀት ውስንነትና በታቀደውም ልክ ቢሆን በወቅቱ ወደ ስራ አለመግባት፤
- ❖ በአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የተሰማራውን ባለሀብት በምርት ጥራት፣ በጊዜና በወጭ ተወዳዳሪ የሚያደርጉ ሳይንሳዊ የድጋፍ ማእቀፎችን አስቀምጦ አለመንቀሳቀስ፤ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ተቀናጅቶ የመስራት ውስንነት፣
- ❖ ባለሙያውና አመራሩ በዘርፉ የተሰማራውን ባለሀብት በበቂ ዝግጅት፣ እውቀትና ክህሎት ላይ የተመሰረተ ድጋፍ አለማድረግና ማብቃት አለመቻል፣ የትኛው ኢንዱስትሪ ምን ድጋፍ ይፈልጋል፣ ድጋፉ ቢሟላለት ምን ፋይዳ አለው ብሎ መለየትና ድጋፍ ማድረግ ላይ ሰፊ ችግር ይስተዋላል፡፡
- ❖ አሜራሩና ባለሙያው ከአዳዲስ ቴክኖሎጅዎች ጋር ለመተዋወቅ፣ ለመላመድና ለማስፋት ራስን ዝግጁ አድርጎ ያለማንቀሳቀስ፣
- ❖ ባለሃብቱ የሚያቋቁማቸውን ፕሮጀክቶችና ኢንዱስትሪዎች በአዳዲስ ቴክኖሎጂ ታግዞ የማስራትና የማምራት ወስንነት መኖር፣
- ❖ የድጋፍ አሰጣጥና የሚረጃ አያያዝ በዕወቀትና በክህሎት ላይ ያልተመሠረተ መሆንና የሚያዘው መረጃ ግልጽነትና ተዓሚኒነት የጎደለው መሆን፣

### 3.1.3. ከአደረጃጀትና አሰራር አኳያ

- ❖ ዘርፉ እንደሃገር በተለይ ደግሞ እንደክልል በጅምር ላይ ያለ በመሆኑ ሃብት ለፈጠሩ ባለሃብቶች ግንዛቤ ፈጥሮ እና ፕሮጀክቶችን ደግፎ ወደ አፈጻጸም እንዲገቡ እንዲሁም የኢንዱስትሪዎችን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ የሚያስችል አደረጃጀትና አሠራር ተደራሽ አለመሆን፣
- ❖ ለባለሃብቶች ፣ ለፕሮጀክቶችና ለኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ድጋፍ በአጋር አካላት የተቀናጀ አሠራር ያልታገዘ መሆን፣
- ❖ የተዘረጋው አደረጃጀትና አሰራር የዕዝ ሰንሰለት የበዛበትና በውጤት ላይ የተመሠረት የድጋፍና ክትትል ሥርዓቱ ደካማ መሆን፣

- የአቅም መገንቢያ አደረጃጀቶችን የአመራሩንና ሙያተኛዉን የመፈጸም አቅም በሚያጠናክር ትኩረትና ብስለት አለመምራት፡፡ በመሆኑም የ1ለ5ና የልማት ቡድን ውይይትና ግምገማ በእምነት ይዞ አለመተግበር ጋር ተያይዞ ይህን ችግር የሚፈታ አለመሆን፣ መማማሪያ ውይቶች የችግር መፍቻ አደረጃጀት አድርጎ አለመጠቀም፣
- የድጋፍ ሂደቱን የተሟላ የሚያደርግ በኢንዱስትሪ ዘርፉ፤ በትምህርት ተቋማት፤ (ዩኒቨርስቲዎችና ሙያናቴክኒክ ኮሌጆች) በኢንዱስትሪያሊስቱ እና በሌሎች አጋር አካላት መካከል የጋራ አሰራርን በማጠናከር የቴክኖሎጅና የአሰራር ችግርን የሚሞላ፣ የመሰረተ ልማትና የብድር አቅርቦቱን የሚያቀላጥፍ መስተጋብር አለመዳበር፣

### 3.1.4. ከግብአትና ማሰረተ ልማት አቅርቦት አኳያ፤

- በዞን፣ በወረዳና በከተማ ላለው አመራርና ባለሙያ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ ግብዓቶች ተሟልተው አለመገኘት፣
- ባለሃብቱ ወደ ዘርፉ እንዲሠማራ የሚያስችል የመሠረተ ልማት አቅርቦት ያለመስፋፋት፣

## ክፍል ሶስት፤ የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች፤

- ለተማሪጠና ሃብት ለፈጠሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በቅድመ ዝግጅት ላይ የተመሠረተ ተከታታይ ግንዛቤ መፍጠርና ወደ ዘርፉ እንዲሠማሩ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረግ፣
  - የተሳታፊ የህብረተሰብ ክፍል በማለየት በዞኖች፣ ከተሞችና ወረዳዎች ቢያንስ በየወሩ አንድ የወይይት መድረክ በማዘጋጀት ተሳታፊዎች በዘርፉ እንዲሠማሩ ማነሳሳት፣
  - ፍላጎት የገለጹትን ተካታታይ ድጋፍ ማድረግና ወደ ዘርፉ እንዲሠማሩ ፈጣንና ቀልጣፉ አሠራር ማዘርጋት
- ለዘርፉ ፕሮጀክቶችና ኢንዱስትሪዎች ችግር ፈች የሆነ የአቅም ግንባታ፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና የካይዘን ትግበራ ላይ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የመጣውን ፋይዳ በግምገማ ማረጋገጥ፣
  - የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተው ወደ ሥራ ያልገቡትን ፕሮጀክቶች ያለባቸውን ችግር በዝርዝር በማጥናት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ችግራቸውን መፍታት
  - የፕሮጀክቶችና ኢንዱስትሪዎችን የቴክኖሎጂ ፍላጎት በማለየት ዝርዝር የቴክኖሎጂ አጠቃቀሞችን ማዘጋጀት፣
  - ካይዘን ለመተግበር ፍላጎት ያላቸውን ኢንዱሰትሪዎች በማለየት የስልጠናና የትግበራ መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረግ

- ለዘርፉ ፕሮጀክቶችና ኢንዱስትሪዎች የሚገጥማቸውን የፋይናንስ ችግር ለመፍታት የተቀማጡ የሊዝ ፋይናንስና የፕሮጀክ ፋይናንስ አሠራሮችን በስፋት ተግባራዊ ማድረግ፣
  - የሊዝና ፕሮጀክት ፋይናንስ ለማጠቀም የሚፈልጉ ኢንዱስትሪዎችና ፕሮጀክቶች የንግድ ዕቅድና የአዋጭነት ጥናት በሚያዘጋጁበት ጊዜ አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ
  - በሊዝ ፋይናንስ ለማጠቀም የሚፈልጉ ኢንዱስትሪዎችንና ፕሮጀክቶችን የቴክኖሎጂ ፍላጎት በማለየት አዋጭና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን ማለየት፣ ማደራጀትና ለተጠቃሚዎች ማድረስ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የግብዓት፣ የአመራረትና የገበያ ችግርን በመፍታት የማምረት አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ ድጋፎችን ማጠናከርና  በየጊዜው እየገመገሙ ኢንዱስትሪዎች የደረሱብትን የማምረት አቅም ማረጋገጥ፣
- የኢንዱስትሪ መሠረተ ልማቶች የተሟሉላቸው ክላስተሮችና ኢንዱስትሪ መንደሮች እንዲለሙ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መሥራት፣
  - በጀት የተመደበላቸውን የክላስትርና የኢንዱስትሪ መንደሮች በወቅቱ ካሳ ከፍሎ ከሶስተኛ ወገን ነጻ በማድረግ ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች ማስተላለፍ፤
  - ክላስተሮችና  ኢንዱስትሪ መንደሮች እንዲስፋፉና እንዲለሙ አዳዲስ ቦታ ማለየትና በከተማው ማስተር ፕላን እንዲካተት ማድረግ፣
  - አሁን ማስራት በማይችልባቸው ክላስተሮች ላይ ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን መልምሎ ማስገባትና ስራ ማስጀመር፣
- የኢንደስትሪዎችን ፕሮፋይል በየጊዜው ማጥራት፣ መተንተንና ለቀጣይ እቅድ በግብዓትነት ማጠቀም፡፡

6. በፌድራል መንግስት በክልሉ መንግስት የሚለሙ የሁለገብና አግሮ ፕሮሰሲንግ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን፣ የክላስተር ሼከላትንና የገጠር ትራንስፎርሜሽን ሼከላትን የካሳ ስሌት እንዲጠናቀቅ በማድረግ ካሰውን በመክፈል መሬቱን ከሦስተኛ ወገን ለማፅዳትና ወደ ልማት ለማስገባት የሚያስችል ድጋፍ ለዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች መስጠት፤
7. ለኢንዱስትሪ ክላስተር የሚዘጋጁ መሬቶችን ሁሉም ከተማ አስተዳደሮችና ወረዳዎች እንዲያዘጋጁ የሚያስችል ድጋፍ መስጠት፤
8. በሁለገብ የኢንዱስትሪ ፓርክ ያሉ ፕሮጀክቶችን መረጃ በማጥራት በየፕሮጀክቶቹ ባህሪ የኢንዱስትሪ አክስንቴሽንና አስተዳደራዊ ድጋፍ ሊያገኙ የሚችሉብትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
9. በቱለፋ ከተማ አስተዳደር የክልሉ መንግስት የብረታ ብረትና ኬሚካል ክላስተር የኢንዱስትሪ ፓርክን ለማቋቋም በዞኑ ከዚህ በፊት ለኢንቨስትመንት መሬት የተሰጣቸውን ፕሮጀክቶች መረጃ ማጥራት፣ ከዚህ

በፊት ወደ ግንባታ ያልገቡ ፕሮጀክቶችን ወደ ተከለለው የኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው እንዲያለሙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

10. ሌሎች የሪፎርም ተግባራትን ማለትም የ1ለ5 ወይይት፣ የልማት ቡድን ወይይትና የመማማርና ዕድገት ፕሮግራምን አጠናክሮ በማስቀጠል የተግባራት ማስፈጸሚያ መሳሪያ አድርጎ ማጠቀም፤